# በግልግል የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮች በኢትዮጵያ-የመወያያ ነጥቦች

በዘካርያስ ቀንዓ*

## 1

## መግቢያ

በልዩነቶች ማስወገጃ አግራጭ መንገድነቱ የግልግል ዳኝነት በዛሬው ዓለም የታወቀ ሆኗል። የግልግል ዳኝነት ሁለት ተዋዋዮች ልዩነቶቻቸውን ወይም አለመግባባቶቻቸውን በመንግሥት የተሾሙ ዳኞች በሚዳኙባቸው ፍርድ ቤቶች ከማቅረብ ይልቅ ባለጉዳዮቹ ለሾሟቸው የግል ዳኞች የሚያቀርቡበት ሥርዓት ነው። በርካታ ባለጉዳዮች ከፍርድ ቤቶች ይልቅ የግልግል ዳኝነትን የሚመርጡበት ምክንያት ጉዳያቸው ራሳቸው በመረጧቸው ዳኞች በመታየቱና የክርክሩ ሂደት ድብቅና ከተከራካሪ ወገኖች ወይም እነርሱ ከወከሏቸው ሰዎችና ከዳኞቹ ውጪ ለማንም ክፍት ባልሆነ መድረክ በመዳኘቱ ነው። ለጥሩ ስማቸውና ለመልካም ዝናቸው የሚጨነቁት ምንጊዜም የክርክሮቻቸውም ሆነ የልዩነቶቻቸው ዝርዝር አደባባይ ወጥተው በመንግሥት ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ አይፈልጉም።[1] በተከራካሪ ወገኖች መካከል የሚነሳውን ክርክር በማስወገጃ መንገድነቱ የግልግል ዳኝነት "ግትር ያልሆነ ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ሊደረግ የሚችል ከዚሁም የተነሣ በፍርድ ቤቶች ከሚደረጉት ሙግቶች ባጠረ ጊዜና በቀለጠፈ ሁኔታ ሙግት ሊያልቅ የሚችልበት ነው" ተብሎ ይወሰዳል።[2]

የዚህ ጽሁፍ ፍላጎትና ዓላማ ስለግልግል ዳኝነት አጠቃላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አይደለም። በሰዎች መካከል የሚከሠቱትን ልዩነቶች ማስወገጃ መንገድነቱን በሚመለከት የግልግል ዳኝነት ስለሚሠጠው ጥቅም በሠፊው ደግፎ ለመቆምም አይደለም። ከርዕሱ ከራሱ መረዳት እንደሚቻለው ፍላጎቱ ወይም ሐሳቡ ከሠፊው የግልግል ዳኝነት ርዕስ ውስጥ በግልግል የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮችን የማየት ሆኖ ያውም ባጠቃላይ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ በማተኮር ነው።

ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት መታየታቸው ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም በሰዎች መካከል የሚነሱት ሁሉም ዓይነት ክርክሮችና አለመግባባቶች ባለጉዳዮቹ በመረጧቸው የግል ዳኞች ወይም ኢክስፐርቶች

---

* የሕግ ሌክቸረር ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፥ ሕግ ፋኩልቲ

1 Allan Redfern and Martin Hunter, Law and Practice of International commercial Arbitration, Sweet and Maxwell, London, 1986 ገጽ 17።

2 ዝኒ ከማሁ።

ሊዳኙ ይችላሉ ማለት ግን አይደለም። የተለያዩ አገሮች በልዩ ልዩ ምክንያቶች አንዳንድ ጉዳዮችን በግልግል ዳኝነት ሊታዩ ከሚችሉት ውጪ ናቸው በማለት ይፈርጁዋቸዋል። በመሆኑም በያንዳንዱ አገር በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች ወይም ክርክሮች ወይም ነገሮች የመኖራቸውን ያህል በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ የማይፈቀዱ ጉዳዮች አሉ። ሬድፈርንና ሀንተር ስለዚህ ነጥብ በጥሩ ሁኔታ ያጠቃለሉትን ከዚህ በታች እጠቅሳለሁ:-

> ያንድ ጉዳይ በግልግል የመዳኘትና ያለመዳኘት ፅንሰ ሐሳብ (አርቢትረቢሊቲ) በአለመግባባቶች ማስወገጃ መንገድነቱ በግልግል ዳኝነት ላይ የተደረገ የፖሊሲ ማዕቀብ ነው። እያንዳንዱ መንግሥት በገዛ ራሱ ፖሊሲ መለኪያ የትኞቹ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉና የትኞቹ እንደማይችሉ መወሰን ይችላል። ውሉን በሚገዛው ሕግ መሠረት ወይም የግልግል ዳኝነቱ በሚደረግበት ቦታ ሕግ መሠረት ወገኖቹ የተስማሙበት ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የማይችል ከሆነ የወገኖቹ ስምምነት ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል ነውና ከመሠረቱ ስምምነቱ ውጤት የማይሰጥ ነው ለማለት ይቻላል። በተጨማሪም ያንድ ግልግል ዳኝነት መድረክ ውሳኔ ተፈጻሚ እንዲሆን በሚፈለግበት አገር ሕግ መሠረት ውሳኔ ያገኘው ጉዳይ ለግልግል ዳኝነት የማይቀርብ ዓይነት ከሆነ ውሳኔው ዕውቅና እንዳያገኝም ሆነ ተፈጻሚ እንዳይሆን ሊከለከል ይችላል።[3]

ከዚህ በላይ ከሠፈረው ጥቅስ ለመረዳት እንደሚቻለው የትኞቹ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉና እንደማይችሉ ብዙውን ጊዜ የሚወሰነው በሀገሮች መንግሥታት ሲሆን ዉሳኔዎቹም የሚገለፁት በብሄራዊ የግልግል ዳኝነት ሕጎች አማካኝነት ነው። በፖሊሲዎች ፥ በብሄራዊ ጥቅሞችና የንግድ እውነታዎች መለያየት የተነሣ በአንዳንድ ሀገሮች በግልግል ሊታዩ የሚችሉት ጉዳዮች በሌሎች ሀገሮች ደግሞ የማይታዩ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። በሌላ አነጋገር በሀገሩ ፖሊሲ ምክንያት በአንዳንድ ሀገሮች አንዳንድ ጉዳዮች በተከራካሪ ወገኖች በሚሾሙ የግል ዳኞች እንዳይዳኙና የግድ በመንግሥት ፍርድ ቤቶች ዳኞች እንዲዳኙ የሚደረጉ መሆናቸውንና ምናልባትም እንደነዚሁ ዓይነቶቹ ጉዳዮች በተከራካሪ ወገኖች በተመረጡ የግል ዳኞች በግልግል ተዳኝተው ቢገኙም ሕገ-ወጥ ተደርገው እንደሚወሰዱና የዳኝነቱም ውሳኔ ተፈጻሚ እንደማይደረግ ይስተዋላል።

በዚህ ውስን ጽሁፍ ውስጥ በኢትዮጵያ የትኞቹ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉና እንደማይችሉ ለመዳሰስ ሙከራ ተደርጓል። ሙከራው በርዕሱ ሥር ሊነሱ የሚችሉትን ነጥቦችን በተሟላ መልኩ አልዳሰሳቸውም። ሙከራው ይልቅስ በኢትዮጵያ ውስጥ የትኞቹ ጉዳዮች በግልግል ሊዳኙ እንደሚችሉና እንደማይችሉ ለፀሐፊው ከተሰማው በመነሳት ጥያቄዎችን ነው የሚያነሳው። ይህ ሙከራ ምናልባት ወደፊት በርዕሱ ላይ የሚደረገውን ምርምር ሊረዳ ይችል ይሆናል የሚል ተስፋ አለ።

---

3 ዝኒ ከማሁ ፥ ገጽ 105።

## 2

## <u>የቤተዘመድ ጉዳዮችና በግልግል ሊታይ ይችላል አይችልም ጥያቄ</u>

በፍ.ብ.ሕ.ቁ.722 ፥ 724 ፥ 729 እና 730 ሥር ከተመለከቱት ጉዳዮች በስተቀር በኢትዮጵያ ውስጥ ካለፍርድ ቤት ወይም ካለዳኞች በስተቀር ሌላ መድረክ የዳኝነት ሥልጣን የለውም ተብሎ በግልጽ የተደነገገላቸው የዋና ሕግ ቁጥሮች የሉም። በእነኚህ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት የፍ.ብ.ሕ. ቁጥሮች ውስጥ ያለው መልዕክት ሲጠቃለል በነኚህ በተጠቀሱት ቁጥሮች ሥር በሚሸፈኑ ጉዳዮች የግልግል ዳኝነትን ጨምሮ ሌላ አማራጭ የክርክር ማስወገጃ መድረክ ፈጽሞ ሥልጣን እንደሌለውና ሥልጣኑ የፍርድ ቤት ብቻ መሆኑን ነው። በሌላ አነጋገር በነኚህ በተዘረዘሩት የሕግ ቁጥሮች ድንበሮች ውስጥ የሚታቀፉ ጉዳዮች በግልግል የሚታዩ አይደሉም ነው።

የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 722 ድንጋጌ መተጫጨት መደረጉን ወይም አለመደረጉን ወይም ስለአንድ ስለተደረገ መተጫጨት በሕግ ፊት የሚፀና መሆን ወይም ያለመሆን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነው እንደማለቱ እነኚህ በቁጥር 722 የተሸፈኑ ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት የሚቀርቡ ጉዳዮች አይደሉም። በሕግ ፊት የሚፀና መተጫጨት መደረግ አለመደረጉ በግል ዳኝነት አይታይም ያሰኘውም "ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው"የሚለው የሕጉ አነጋገር ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.724 መሠረትም ጋብቻ መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙን ወይም አንድ ጋብቻ በሕግ ፊት የሚፀና መሆኑን ወይም አለመሆኑን አስመልክተው የሚነሱ ክርክሮች ለግልግል ዳኞች እንዳይቀርቡ ሕጉ "በነኚህ ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው" በማለት ከልክሏል ለማለት ይቻላል። ከዚህ ባልተለየ ሁኔታ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.730 መሠረትም በሁለት ሰዎች መካከል ከጋብቻ ውጭ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መኖሩን ወይም ያለመኖሩን ለመወሰን ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ብቻ መሆኑን በመደንገግ ሕጉ አቋም ወስዷል። በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ አብረው እያሉ በተጋቢ ወገኖች መካከል የሚነሱ ችግሮች ወይም አለመግባባቶች እንደዚሁም በሁለቱም ተጋቢዎች በጋራ ሆነ ባንደኛው ተጋቢ ወገን በተናጠል የሚቀርቡ የፍቺ አቤቱታዎች የግድ ለግልግል ዳኝነት የሚቀርቡ ቢሆኑም ከጋብቻ ውጪ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች ወይም አለመግባባቶች ግን በፍርድ ቤት እንጂ በሌላ በማንኛውም መድረክ ሊዳኙ አይችሉም።

ምንም እንኳን ከቁጥር 725 እስከ 728 ባሉት አዛዥ የፍ.ብ.ሕ. ድንጋጌዎች መሠረት በጋብቻ ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች ፥ የፍቺ አቤቱታዎች እንደዚሁም ከፍቺ የሚነሱ ክርክሮች የግድ ለሽምግልና ዳኝነት የሚቀርቡ ጉዳዮች ቢሆኑም ፥ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.729 ሥር በተደነገገው መሠረት የመፋታት ውሳኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሥልጣን ያላቸው ግን ዳኞች ብቻ ናቸው። የፍ.ብ.ሕ.ቁ.729 ያለው መልዕክት የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሚሰጡት የፍቺ ውሳኔ የግድ ለፍርድ ቤት (ለዳኞች) መቅረብ ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ሊሆን ሲችል በዚህም መልዕክት መሠረት ፍርድ ቤቶች ወይም ዳኞች የፍቺ ውሳኔ ባግባቡ በተቋቋመ የግልግል ዳኝነት መድረክ የተሰጠና ሕግ የሚጠይቀውንም ሁሉ አሟልቶ የተሰጠ መሆኑን ሲያረጋግጡ ተቀባይነት ያለውና ተፈጻሚ ሊሆን የሚችል ውሳኔ መሰጠቱን በማረጋገጥ የራሳቸውን ውሳኔ ይሰጣሉ የሚል ሆኖ ይገኛል። በአንድ በኩል ፍርድ ቤቶች ወይም ዳኞች

ይህን ውሳኔ የሚሰጡት ሕጉን ተንተርሰው በራሳቸው አነሳሽነት ቢሆንም በሌላ በኩልና ከዚሁ ለየት ባለ መልኩ በአንድ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኝነት መድረክ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በጉቦ ይሁን ወይም በሌላ የሽምግልና ዳኞቹ አድሏዊነት የተነሣ ወይም በ3ኛ ወገኖች ተንኮል ምክንያት ወይም የሽምግልና ዳኞቹ ውሳኔ በሕግ ፊት ወይም ለአመዛዛኝ ኅሊና በግልጽ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑ የተነሣ ይግባኝ ለፍርድ ቤት ዳኞች መቅረብ እንደሚችልም ተደንግጎ ይገኛል።[4] የፍ.ብ.ሕ.ቁ.729 መልዕክት ከሌላ አቅጣጫ ሲታይ የፍርድ ቤት ዳኞች ሚና የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የሰጡትን ውሳኔ ተቀብሎ የማጽደቅና ከዚያም ማረጋገጫ የመስጠትም ይመስላል። በሌላ አነጋገር አንድ የጋብቻ ግንኙነት መፍረሱን ወይም በጋብቻ ውስጥ የነበሩ ተጋቢ ወገኖች መፋታታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ መስጠት የሚችለው ፍርድ ቤት እንጂ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኝነት መድረክ ወይም ውሳኔ የሰጡት ዳኞች በግል አለመሆኑን ነው የፍ.ብ.ሕ.ቁ.729 የሚነግረን። ቁጥር 729 ይህን የኋለኛውን መልዕክት ነው የሚያስተላልፈው ለማለት የሚያስደፍረው በተለይም ኦፊሲየላዊ የሆነው የቁጥር 729 የአማርኛው ቅጂ ድንጋጌ ነው።[5]

## 3

## የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ውሎች - ለግልግል አይቀርቡ ይሆን ?

መሠረታዊውን (ዋናውን) ሕግ ከማየት ሥነ ሥርዓታዊውን ወደ ማየቱ ሲኬድ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 315(2) ሥር በሕግ የተከለከለ ጉዳይ ወይም የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በግልግል ሊታዩ እንደማይችሉ ተደንግጎ ይሰተዋላል። በዚህ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ315(2) ሥር ከተጻፈው በመነሳትም ታዲያ እንዲህ ከሆነ በሕግ ከተከለከሉትና ከአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ውሎች ከሚነሱ ወይም ከነዚህ ጋር ከተያያዙ ጉዳዮች በስተቀር ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ በፍ.ብ.ሕ.ከቁጥር 3325 እስከ 3346 የተጻፉት እንደተጠበቀ ሆነው ፥ ለግልግል ሊቀርቡ የሚችሉ ወይም በግልግል ሊታዩ የሚችሉ ናቸው ማለት ነው ? የሚል ጥያቄ ማስከተሉ አይቀርም። በመጀመሪያ ደረጃ:-

> "በግልግል እንዳይወሰን በሕግ የተከለከለ ጉዳይ ወይም በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3131 እንደተነገረው ያለ ጉዳይ ሲሆን ለግልግል ዳኝነት አይቀርብም።"

የሚል ድንጋጌ በፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ውስጥ ተጽፎ መገኘቱና እንዲህ የሚል ቃል ወይም ይህን የሚመስል ድንጋጌ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ባሉት የፍትሐ ብሄር ሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ ተጽፎ ያለመገኘቱ የሚገርም ነው።

በሌላም በኩል በሁለቱ የሕግ ቁጥሮች መልዕክቶች ማለትም በአንድ በኩል በፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 እና በሌላ በኩል በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 315(2) መካከል ያለው ልዩነት የአተረጓጎም ጥያቄንም ሊያስነሣ ይችላል። በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁጥር 315(4) ሥር "በዚህ ምዕራፍ የተነገሩት ድንጋጌዎች በፍ.ብ.ሕ. ከቁጥር 3325 እስከ 3346 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች

---

4 በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 736።

5 የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 729 የአማርኛው ቅጂ እንዲህ ይነበባል:- "የመፋታት ውሳኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሥልጣን ያላቸው ዳኞች ናቸው።"

የሚነኩ አይደሉም" ተብሎ የተጻፈው ሲታይ የአተረጓጎም ጥያቄ ማስነሳቱን ይበልጥ ያጎላዋል። ታዲያ በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በአራተኛው መጽሐፍ አራተኛው ምዕራፍ ውስጥ ከተጻፉት ድንጋጌዎች ውስጥ በፍትሐ ብሄር ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 የተጻፉትን የሚነካ በተለይም ደግሞ በፍትሐ ብሄር ሕጉ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ከተጻፉት ውስጥ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ከሚዋዋሏቸው ውሎች የሚነሱት ጉዳዮች ለግልግል አይቀርቡም የሚል ከሌለ የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 315(2) ድንጋጌ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል ? በሌላ አነጋገር የበላይነት ባላቸው ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ባሉት የፍ.ብ.ሕ. ቁጥሮች ውስጥ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች የሚነሱ ክርክሮች በግልግል ሊታዩ እንደሚችሉ ወይም እንደማይችሉ የተጻፈ ነገር ከሌለ ይህ ራሱ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች የሚነሱት ክርክሮች በግልግል ሊታዩ እንደሚችሉ ያመለክታል ተብሎ ሊወሰድ አይችል ? ወይንስ በፍ.ብ.ሕ. ከቁጥር 3325 3346 የተጻፉት የበላይነት እንዲኖራቸው በሁለቱ ሕጎች አግባብ ባላቸው ቁጥሮች መካከል ግልጽ ተቃርኖ መኖር አስፈላጊ ይሆን ?

በከሣሽ የመጠጥ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን እና በተከሣሽ በኩንዳን ሲንግ ኮንስትራክሽን ሊሚትድ[6] መካከል በተደረገው ክርክር ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 315(2) የተጻፈው ከአስተዳደር ውሎች ጋር የተያያዙ ክርክሮች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ ከሚችሉ ጉዳዮች ጎራ ውጪ እንደሆነ የሚናገር እንደበቂ ድንጋጌ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል የሚል አቋም ወስዷል። በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ይህን አቋም የወሰደበት ምክንያት ጠጋ ተብሎ ሲጤን የፍ.ሥ.ሥ ሕግ ቁጥር 315(2) ድንጋጌ ከአስተዳደር ውሎች የሚነሱ ክርክሮች በግልግል እንዳይታዩ እንደሚከለክል እንደበቂ የሕግ ድንጋጌ ከመውሰዱ ይልቅ በዳኝነት ሥልጣን ጥያቄ ላይ በተመሠረተ ምክንያት መሆኑን መረዳት ይቻላል። የወሰደውን አቋም ትክክለኛነት ለማሳመን ሲጥር ፍርድ ቤቱ "የትኛው ፍርድ ቤት ወይም መድረክ አንድን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን እንዳለው የመወሰን ድርሻ የሥነ ሥርዓት ሕግ እንጂ የፍትሐ ብሄር ሕግ አይደለም"[7] ብሏል። ፍርድ ቤቱ ይህን ከዚህ በላይ የተመለከተውን ማሳመኛ ያራመደበት ዋናው ምክንያት በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 315(4) ሥር "በዚህ ምዕራፍ የተነገሩት ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 3325 እስከ 3346 የተጻፉትን የሚነኩ አይደሉም" ተብሎ የተጻፈውን ትልቅ ነጥብ ለማክሰስ ይመስላል። በዚህም አቋሙ ፍርድ ቤቱ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 3325 እስከ 3346 ከተጻፉት ውስጥ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጓቸው ውሎች በግልግል ሊታዩ አይችሉም የሚል ድንጋጌ ከሌለ የፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 315(2) ድንጋጌ ተግባራዊ መደረግ የለበትም በማለት ተከሣሽ ያነሳውን ክርክር እንዳልተቀበለ ነው የገለጸው።

የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ከሚያደርጓቸው ውሎች የሚነሱ ክርክሮች በግልግል እንዳይታዩ ተከልክሏል የሚለውን አቋሙን ለማጠናከር ፍርድ ቤቱ ያነሳው ሌላው ነጥብ በፍትሐ ብሄር ሕጋችን ውስጥ የተካተቱት የአስተዳደር ውሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከፈረንሳይ ሕግ

---

[6] ከሣሽ የመጠጥ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን -በ- ተከሣሽ የኩንዳን ሲንግ ኮንስትራክሽን ሊሚትድ ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሄር መዝገብ ቁጥር 688/79 ፣ (ያልታተመ)።

[7] ዝኒ ከማሁ።

መወሰዳቸውን ነው። በዚህ ረገድ ፣ፍርድ ቤቱ ያነሳው ተጨማሪ ነጥብ በፈረንሳይ ሕግ መሠረት የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች የሚያደርጓቸው ውሎች በግልግል እንዳይታዩ የተከለከለ መሆኑንና ክልከላውም የተጻፈው በፈረንሳይ የፍትሐ ብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ መሆኑን ሲሆን በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕጋችን ቁጥር 315(2) የተጻፈው ክልከላ የኛ የአስተዳደር ውሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ከተወሰዱበት ምንጭ አኳያ ሲታይ ትክክል ነው በማለት ይደመድማል።

የፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 315(2) እና 315(4) ባንድ በኩል እና የፍ.ብ.ሕ. ከቁጥር 3325 እስከ 3346 በሌላ በኩል ያለመጣጣምን በሚመለከት ሌላም የአተረጓጎም መርሕ ነጥብ ማንሳት ሲቻል ይኸውም ባንድ ጉዳይ ላይ በኋላ የወጣው ሕግ ቀድሞ የወጣውን ሕግ በውስጠ ታዋቂነት በመሻር የበላይነት እንደሚኖረው ሲሆን በዚህ የአተረጓጎም መርሕ ከተሄደ በ1958 ዓ.ም የወጣው የፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ በ1952 በወጣው የፍትሐ ብሄር ሕግ ላይ የበላይነት ይኖረዋል ለማለት ይቻላል። በነገራችን ላይ ይህን ነጥብ ፍርድ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው በመጠጥ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣንና በኩንዳን ሲንግ ኮንስትራክሽን ሊሚትድ መካከል በተደረገው ክስ ውሳኔ ውስጥ አንስቶታል።

ሌላ ጥያቄ ልጨምር። ሁለቱ ያልተጣጣሙትና የሚጋጩ የሚመስሉት የሕግ ቁጥሮች ማለትም ባንድ በኩል ከ3325 እስከ 3346 ያሉት የፍ.ብ.ሕ. ቁጥሮች እና በሌላ በኩል የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.315(2) የፊተኞቹ ቁጥሮች በአዋጅ ውስጥ የኋለኛው ቁጥር ደግሞ በንጉሠ ነገሥታዊ ድንጋጌ ውስጥ መገኘት በሕጎች ደረጃ ላይ በሚመሠረተው የሕጎች አተረጓጎም መርሕ እንድንጠቀም ምክንያት ሊሆነን ይችል ይሆን ?

## 4

## ግልግልን የሚጠቁሙ ሌሎች የመሠረታዊ ሕግ ቁጥሮች

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ በግልግል የሚታዩና የማይታዩ ጉዳዮችን በሚመለከት ዋናው ችግር የሚመነጨው የፍትሐ ብሄር ፣ የንግድና የባሕር ሕግ አንዳንድ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ በግልጽ ከመደንገጋቸውና ስለብዙ ጉዳዮች ግን ዝም ከማለታቸው ይመስላል። በፍ.ብ. ሕጉ መሠረት የቤተዘመድ ክርክሮች በግልግል ዳኝነት መታየት በተከራካሪ ወገኖች ምርጫና ፈቃድ ሳይሆን የግዴታ[8] ሆኖ ስናገኘው በሌላ በኩል ግን ለምሳሌ በ1952 ዓ.ም. በወጣው በፍትሐ ብሄር ሕጉ ውስጥ ስለግልግል በቁጥር 941 ፣ 945 ፣ 969(3) ፣ 1275 ፣ 1472 እና ተከታታዮቹ 1534(3) ፣

8 ሐምሌ 14 ቀን 1969 ዓ.ም በወቅቱ ተቀዳሚ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ኃይሉ ይመኑ ባወጡት መመሪያ ቁጥር 2756/ፊ1ሀ/20 መሠረት በኢትዮጵያ በመንግሥት የልማት ሥራ ድርጅቶች መካከል የሚነሣ የፍትሐ ብሄር ክርክር በግድ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ተደርጎ ነበር።

1539(2) ፥ 1765 እና 2271[9] ሲጠቀም በሌላ ቦታ ግን የለም።

በንግድ ሕጉ ውስጥም ስለግልግል በግልጽ የተጻፈባቸውበቁጥር 267 ፥ 295 እና 303 ቁጥር 267ን በማጣቀስ 500(1) ፥ 647(3) ፥ 1038 ፥ 1103(3) ሲሆን በባሕር ሕጉ ውስጥ ስለግልግል በግልጽ የተጻፈው በአንድ ቁጥር ሥር ብቻ ሲሆን እርሱም ቁጥር 209 ነው።

በሌላ አቅጣጫ ላለፉት ሁለት አሥርታትያህል ተፈጻሚ በነበረው የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ማለትም በአዋጅ ቁጥር 64/1968[10] በቁጥር 101(1) ሥር የወልም ሆነ የግል የሥራ ክርክር በግልግል ዳኝነት ሊታይ እንደሚችል ተመልክቶ እንደነበር ሲታወስ ፥ በዚሁ በተጠቀሰው አዋጅ በቁጥር 101 ንዑስ ቁጥር (3) ሥር የሠራተኛ ማሕበራት ባልተቋቋሙባቸው ድርጅቶች ውስጥ ክርክሮችን ለግልግል ዳኝነት ማቅረብ በፍላጎትና በምርጫ ሳይሆን በግድ እንደነበረ ይስተዋላል። በአዲሱ የሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ማለትም በአዋጅ ቁጥር 42/1985[11] ውስጥም በቁጥር 143(1) ሥር "የሥራ ክርክር ተካፋይ የሆኑ ወገኖች ጉዳያቸውን ራሳቸው በመረጡት በግልግል ዳኛ ወይም ..... አይከለከሉም" ተብሎ ተደንግጓል።

የሠራተኛ አዋጆችን ድንጋጌዎች እንኳን ባይጨምር ከላይ በተመለከቱት በሌሎች ሕጎች ውስጥ በተዘረዘሩት ቁጥሮች ስለግልግል በግልጽ መደንገጉ ሌሎቹ ሕጎቹ ግልግልን በግልጽ ያላነሱባቸው ጉዳዮች ሁሉ በግልግል ሊታዩ አይችሉም ማለት ይሆን ? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ አግባብ ያለው ነው። ሕጎቹ ላንዳንድ ጉዳዮች ብቻ ግልግልን እንዲያነሱ ያደረጋቸው ምንድነው ? ምክንያቱ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው ሁሉም በፍርድ ቤት እንዲታይ ከማድረግ ይልቅ የግልግል ዳኝነት አማራጭ መኖሩን እንዲያውቁ ለማሳሰብ ይሆን ? ወይንስ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.315(2) ሥር ከሚነበበው በስተቀር በፍ.ብ.ሕ. ከ3325 እስከ 3346 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ በፖለሲ ደረጃ በግልግል ሊታዩ የሚችሉና የማይችሉ ጉዳዮች ባለመገለጻቸው ምክንያት ሰዎች ግራ እንዳይገባቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ የሚመላለሰውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ነው ሕጎቹ ለአንዳንድ ጉዳዮች ብቻ ግልግልን የጠቀሙት ?

በአንዳንድ አገሮች በግልግል ሊታዩ አይችሉም ተብለው በፖሊሲ ደረጃ የሚለዩ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ በጀርመን የፍ.ሥ.ሥ.ሕ. በቁጥር $1025_a$ ሥር የሚከተለው ተደንግጓል ፡- "የከፍሎችን ማከራየት የሚመለከቱ ውሎች መደረጋቸውን ወይም አለመደረጋቸውን አስመልክቶ

---

[9] በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3325 ለግልግል በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት የፍ.ብ.ሕ. 2271 በእርግጥ ግልግልን ለማመልከት የተጻፈ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ለመሸጥ ፈላጊና ለመግዛት ፈላጊ ተስማምተው የዕቃውን ዋጋ ሌላ ሽማግሌ እንዲገምትላቸው ማድረጋቸው በመካከላቸው አለመግባባት ኖሮ ይህንኑ አለመግባባት ለመፍታት ወደ ግልግል መሄዳቸውን አያመለክትም። ዋጋ ተማኝ ሽማግሌ የሚተምነው ዋጋም ቢሆን በግልግል ዳኝነት እንደሚሰጥ ውሳኔ ሊሸጥ የሚፈልገውንና ሊገዛ የሚፈልገውን ወገን ያስገድዳቸዋል ማለት አይደለም።

[10] ነጋሪት ጋዜጣ 35ኛው ዓመት ቁጥር 11።

[11] ነጋሪት ጋዜጣ 52ኛው ዓመት ቁጥር 27።

የሚነሱትን ክርክሮች በግልግል እንዲታዩ ማድረግ ፍርሰና ዋጋ የሌለው ነው። በግልግል እንዲታይ የሚደረገው ስምምነት በጀርመን የፍትሐ ብሔር ሕግ 556[a] ኛው ክፍል በ8ኛው አንቀጽ ሥር በተጻፈው መሠረት ከሆነ ከዚህ በላይ የተጻፈው ተፈጻሚ አይሆንም"[12] ይላል።

በሌላ በኩል የፈረንሳይ የፍትሐ ብሄር ሕግ በቁጥር 2060 ሥር የሚከተለውን ደንግጓል

> የሰዎችን ፍትሐ ብሄራዊ ሁኔታና ችሎታቸውን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን እንደዚሁም ፍቺን ወይም በጋዎች ውሳኔ ለጊዜው መለያየትን ፣ የሕዝብ የጋራ ንብረቶችን እና የሕዝብ ተቋሞችን እንዲሁም ባጠቃላይ መልኩ የሕዝብን ፖሊሲ የሚመለከቱ ጉዳዮችን በግልግል እንዲታዩ ማድረግ አይቻልም።[13]

በጣሊያን በፍትሐ ብሄር ሕጉ በቁጥር 409 ሥር ከተጻፈውና የሥራ ክርክርን ከሚመለከተው እንደዚሁም በቁጥር 442 ሥር ማሕበራዊ ዋስትናንና የግዴታ ሕክምና ዕርዳታን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር ተከራካሪ ወገኖች ማንኛውንም በመካከላቸው የሚነሣውን ክርክር በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ማድረግ ይችላሉ።[14]

ሌሎች አገሮች ከጀርመንና ከፈረንሳይ የተለየ አቀራረብን ይከተላሉ። ለምሣሌ ተሻሽሎ እ.ኤ.አ ከጥር 1 ቀን 1984 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የስዊድኑ የ1929 የግልግል ዳኝነት ሕግ በክፍል አንድ ሥር :-

> ማንኛውም ፍትሐ ብሄር ነክ የሆነና በስምምነት ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ እንደዚሁም በወንጀል ምክንያት የሚነሣ የጉዳት ካሣ ጥያቄ በባለጉዳዮች መካከል ክርክር ያስነሣ ከሆነ በተከራካሪዎቹ ስምምነት በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የግልግል ዳኞች እንዲታይ ማድረግ ይቻላል።[15]

በማለት ደንግጓል።

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ መጋቢት 27/ነሐሴ 29 ቀን 1969 ዓ.ም የወጣው የስዊስ ኢንተርካንቶናል የግልግል ዳኝነት ሕግ በቁጥር 5 ሥር "ጉዳዩ በአዛዥ የሕግ አንቀጽ ድንጋጌ ምክንያት በመንግሥት የብቻ ሥልጣን ሥር የሚሸፈን ካልሆነ በስተቀር ባለጉዳዮቹ እንደፈለጉና በነፃ ሊያ[illegible]

---

[12] Ottoarndt Glosner, Commercial Arbitration in the Federal Republic of Germany. Kluwer, 1984, በገጽ 42 ላይ የተጠቀሰ።

[13] Jean Louis Delvolve, Arbitration in France, the French law of National and International Arbitration, Kluwer, Deventher, The Netherlands, 1982, በገጽ 61 ላይ የተጠቀሰ።

[14] Italian Code of Civil Procedure ቁጥር 806 School of International Arbitration, Centre for Commercial Law Studies, Queen Mary College, ለ 1987 88 ከዘጋጀው ማስተማሪያ ማቴሪያል በገጽ 91 ላይ የተገኘ።

[15] ዝኒ ከማሁ ገጽ 99።

የሚችሉት ማንኛውም መብት በግልግል ዳኝነት ሊታይ ይችላል"[16] ብሎ ይደነግጋል።

ወደ ኢትዮጵያ ሕግ መለስ ስንል በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 315(2) ሥር ከተጻፈው በስተቀር ሌላ ድንጋጌ በሌለበት የትኞቹ ጉዳዮች በግልግል ሊታዩ እንደሚችሉና እንደማይችሉ የምንወስነው እንዴት ይሆናል ? በተለይም የሕጎችን ለአንዳንድ ጉዳዮች ብቻ ግልግልን መጠቆም እንዴት ነው ማየት የሚገባን? በፍ.ብ.ሕጉ ውስጥ በግልጽ ለግልግል ዳኝነት ይቀርባሉ የተባሉት ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎቹ ሕጎች ዝም ያሉባቸው በርካታ ጉዳዮች ለግልግል እንዳይቀርቡ ተፈልጓል ብለን አቋም መውሰድ እንችላለን ? ወይንስ በፍ.ብ. ሕጋችን በቁጥር 3326(1) የተጻፈውንና በስዊድኑ ሕግ ለተመለከተው የሚቀርበውን መመዘኛ ወስደን "በኢትዮጵያ ባለጉዳዮቹ ያለዋጋ ሊያስተላልፉ የሚችሉትን መብት የሚመለከት ማንኛውም ጉዳይ በግልግል ሊታይ ይችላል" እንበል ? ይህ መመዘኛ ብዙም የማይሠራ መሆኑ በፍ.ብ.ሕ.ቁ 3327(1) ሥር "ከዚህ በላይ ያለው ቁጥር ድንጋጌዎች ይህ ሕግ ለሽምግልና ዳኝነት እንዲቀርብ በግልጽ ባዘዘው ጉዳይ ተፈጻሚ አይሆኑም" ተብሎ የተጻፈው ሲነበብ ወዲያውኑ ይደረስበታል። በመሆኑም ሕጎቹ አንድ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ በግልጽ ሲደነግጉ ያንን ጉዳይ የሚመለከተውን መብት ያለዋጋ የማስተላለፍ ችሎታ የማይጠይቅ ከሆነ "ባለጉዳዮች ያለዋጋ ሊያስተላልፉ የሚችሉትን መብት የሚመለከት ማንኛውም ጉዳይ በግልግል ሊታይ ይችላል" የሚለው መመዘኛ ሁልጊዜ የማይሠራ መመዘኛ ይሆናል።

በተጨማሪም ሕግ አውጪው ለአንዳንድ ጉዳዮች ግልግልን የመጠቆሙንና ለሌሎች ዝም የማለቱን አካሄድ ራሱን ስናይ በሕጎች ውስጥ ግልግል በግልጽ ያልተጠቀሱባቸው በርካታ ጉዳዮች በግልግል ሊታዩ የሚችሉ ናቸው ብሎ ማለት ይቻላል። በመሆኑም በስዊድን ሕግ ውስጥ የተከተተው መመዘኛ ጉዳዩን ከሚመለከተውና አሁን ካለው የኢትዮጵያ ሕግ አኳያ ይሠራል ብዬ አላስብም። የስዊድኖቹን ወይም የነርሱን የሚመስል መመዘኛ ሙሉ በሙሉ መርሳት አለብን እንኳን ባይባል መመዘኛው ለኛ ሁኔታ በጥንቃቄ መታየት የሚገባው ነው። በሕጉቹ ውስጥ ግልግል በግልጽ ያልተጠቀሱባቸው ጉዳዮችም በግልግል የሚታዩ አይደሉም ብሎ መደምደም ልክ ያለመሆኑን ከዚህ በላይ ከተነሣው ክርክር መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም የተነሣ በሕጎቹ ውስጥ ስለአንዳንድ ጉዳዮች ግልግል በግልጽ መጠቀሱ ከፍርድ ቤቶች ይልቅ የግልግል አማራጭ መኖሩን ለባለጉዳዮቹ ለመጠቆም ወይም ባለጉዳዮቹ ክርክሮቻቸውን ለግልግል ዳኝነት እንዲያቀርቡ ለማበረታታት ነው ተብሎ ከመወሰድ የሚያልፍ አይደለም ብሎ መከራከር የሚቻል ይመስለኛል።

በፍ.ሥ.ሥ.ሕ. ቁጥር 315(2) ሥር ከተደነገገው መልዕክት በስተቀር የጀርመን ፥ የጣሊያን ፥ የፈረንሳይ የግልግል ዳኝነት ሕጎች መመዘኛዎችም ቢሆኑ አሁን ካለው የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት ሕግ ጋር እምብዛም የሚጣጣሙ አይመስሉም።

---

16 ዝኒ ከማሁ ገጽ 109።

## የከፍተኛው ፍርድ ቤት የብቻ የሥረ - ነገር ዳኝነት ሥልጣን እና በግልግል ሊታይ ይችላል አይችልም ጥያቄ

በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ከሀ እስከ ቀ የተዘረዘሩት ጉዳዮች በግልግል ሊታዩ የማይችሉ ናቸው ብሎ መከራከር ይቻል እንደሆነ በዚህ ደረጃ ማየቱ አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርም። በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር ግልጽ የሆነ አንድ ነጥብ አለ። ይኸውም ከሀ እስከ ቀ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ሌላ ማንኛውም ፍርድ ቤት የሌለውን የብቻና የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዳለው ነው። ታዲያ ይህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ካልሆነ በስተቀር ሌሎችን ፍርድ ቤቶች ሁሉ የመገደብ የማግለል አቋም በግልግል ዳኝነትም ላይ ተፈጻሚ ይሆን ? ገደቡን ከመድረክ አንፃር ብንመለከተው በተዘረዘሩት ጉዳዮች ሌሎች ፍርድ ቤቶች ብቻ ናቸው የተገደቡት ወይንስ የግልግል ዳኝነት መድረኮችም ጭምር ናቸው? ከሁሉም በላይ በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር የተዘረዘሩት ጉዳዮች ሁሉም በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ጭምር ታስቦ ይሆን ድንጋጌው ያስፈለገው ? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም።

የፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕጉ አንደኛው መጽሐፍ ሁለተኛው ምዕራፍ የፍርድ ቤቶችን የሥረ - ነገር የዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት ሲሆን በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ተካትቶ የሚገኘው የቁጥር 15(2) ድንጋጌዎችም ቢሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 12(1) ሥርና በሁለቱ ተከታይ ቁጥሮች እንደዚሁም በቁጥር 15(1) የተጻፉትን በልዩነት ለመምራት የተጻፉ ሆነው እናገኛቸዋለን።

በሌላ አነጋገር በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር ከሀ እስከ ቀ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚነሱ ክርክሮች ከተንቀሳቃሽ ነገሮች ረገድ ግምታቸው ብር 5,000 ወይም ከዚያ በታች መሆኑ እግምት ውስጥ ሳይገባ ፣ በማይንቀሳቀሱ ንብረቶችም ረገድ ግምታቸው ብር 10,000 ወይም ከዚያ ቤታች በሆኑ እግምት ውስጥ ሳይገባ ለምሳሌ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስለቅቆ ለሕዝብ አገልግሎት የማዋል ክስን በተመለከተ ቁጥር 15(2) የሥረ ነገር ዳኝነትን ሥልጣን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይሰጣል።

በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር ያለው ግልጽ መልዕክት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በዚህ የሕግ ቁጥር ከሀ እስከ ቀ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ለብቻ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያገኘው ሕግ ራሱ ለአውራጃና ለወረዳ ፍርድ ቤቶች የሰጠውን የሥረ ነገር ሥልጣን መልሶ ስለወሰደባቸው መሆኑን ነው። የፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ግልጽ መልዕክት ግን ቀጥሎ ለተመለከቱትም ሆነ ሌሎች መሰል ጥያቄዎች መልስ አይሰጥም። በፍ.ብ.ሥ.ሥ. ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ባንደኛው ላይ ተንተርሶ በመካከላችን አለመግባባት ቢነሳ በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል ብለው ባለጉዳዮች ቢስማሙስ ? የወደፊቱን ልዩነት ወይም ክርክር አስመልክቶ ሳይሆን በቁጥር 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ካንደኛው ላይ የተነሣውንና ያለ ክርክራቸውን በግልግል ዳኝነት እንዲታይላቸው ተከራካሪዎች ቢስማሙስ ? ስምምነቶቹ ሕገወጥ ወይም ተፈፃሚ ሊሆኑ የማይችሉ ናቸው ሊባል ነው ? ባለጉዳዮች አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በቁጥር 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ካንደኛው የተነሣውን ክርክር በሽምግልና ዳኝነት እንዲታይ ተስማምተው እያለ የሽምግልና ዳኝነቱን

መድረክ ለማቋቋም አስፈላጊ በሆነው በዳኞች አሿሿም ላይ ሳይስማሙ ቀርተው በፍ/ቤት ዕርዳታ የግልግል ዳኞች ተሰይመው ክርክሩ እንዲቀጥል ለማድረግ ወደ ፍ/ቤት ቢሄዱ ፍ/ቤቱ በግልግል እንዲዳኝ የተስማማችሁበት ጉዳይ የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን የከፍተኛው ፍ/ቤት ብቻ ስለሆነ ስምምነታችሁን ለመተግበር አልተባበራችሁም ሊላቸው ነው ? በባለጉዳዮቹ በራሳቸውም ይሁን በፍ/ቤት ዕርዳታ የተቋቋመ የግልግል ዳኝነት ፓነል ራሱ የዚህ በግልግል እንዳየው የቀረበልኝ ጉዳይ የሥር-ነገር ዳኝነት ሥልጣን የከፍተኛው ፍ/ቤት ስለሆነ ክርክራችሁን ወደዚያው ውሰዱት እኔ ላይላችሁ አልችልም ብሎ ተከራካሪዎቹን ሊያሰናብት ነው ? ወይንስ ባለጉዳዮቹ ከሾሙኝ ሥልጣን አለኝ ብሎ አከራክሮ ውሳኔ ሊሰጥ ነው ? በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 15(2) ሥር ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ካንደኛው የመነጨ ጉዳይ ለግልግል ዳኝነት ቀርቦ ውሳኔም ተሰጥቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲፈፀም ለአንድ ፍ/ቤት ማመልከቻ ቢቀርብ እንዲያስፈጽም የተጠየቀው ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ ያስፈጽማል ወይንስ ፊቱኑ ጉዳዩ ለከፍተኛው ፍ/ቤት እንጂ ለግልግል ዳኝነት መቅረብ ያልነበረበት ነው በማለት የማስፈፀሙን ጥያቄ አልቀበልም ይላል ? እነኚህና ሌሎችም መሠል ሁኔታዎች በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ድንጋጌና በግልግል ሊታይ ይችላል ወይንስ አይችልም ጋር በተያያዘ ሊነሱ ይችላሉ።

ምናልባት በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 15(2) ከሀ እስከ ቀ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ለከፍተኛው ፍ/ቤት የብቻ የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን መስጠት ለምን እንዳስፈለገ ምክንያቱን መፈለጉና ማወቁ ከላይ ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ ሊሆን ይችል ይሆን ? ከፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 15(2) በስተጀርባ ያለው ዓላማ እነኚህ በዚህ የሕግ ንዑስ ቁጥር የተዘረዘሩ ጉዳዮች ደረጃው ከፍ ባለና ከፍተኛ ሥልጠና ያገኙ ዳኞች በሚያስችሉበት ፍ/ቤት እንዲታዩ የማድረግ ይሆን ? ወይንስ ሕጉ ከዚህም የላቀ ዓላማ ኖሮት ነው ? በቁ. 15(2) በተዘረዘሩ ጉዳዮች ላይ የብቻ የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን ለከፍተኛው ፍ/ቤት መስጠቱ ለንግድና በባሕር ላይ ለሚደረጉ ግንኙነቶች እንዲሁም ላንዳንድ ልዩ ጥንቃቄ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት በነኚህ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡት የሕግ አተረጓጎሞች ውጤታቸሁ አስቀድሞ ሊታወቅ የሚችልና አንድ ወጥ እንዲሆኑ በዚህም ሳቢያ በቁ.15(2) ከተዘረዘሩ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሕጎች እንዲዳብሩ ለማድረግ ይሆን?

ከላይ ጠቆም እንደተደረገው በተዘረዘሩት ጉዳዮች ለከፍተኛው ፍ/ቤት ለብቻ የሥረ-ነገር የዳኝነት ሥልጣን እንዲኖረው ያስፈለገበት ምክንያት ጉዳዮቹ ከፍተኛ ሥልጠና ባገኙና ልምድ ባላቸው ዳኞች እንዲታዩ ከማሰብና ከማመቻቸት ሊሆን ይችላል። የብቻ የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን የመስጠቱ ምክንያት ይህ ከሆነ በቁ. 15(2) ሥር የተዘረዘሩ ጉዳዮች ሁሉም በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ተፈልጎ ነው ለማለት ያስቸግራል ምክንያቱም በዘመናዊው ዓለም የግልግል ዳኞችም ቢሆኑ ማንኛውንም የተወሳሰበ ጉዳይ ለመፍታት አስፈላጊው ችሎታ አላቸውና። በነገራችን ላይ የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 3325(1) ግልጽ እንደሚያደርገው የግልግል ዳኞች ሚቀርብላቸውን ጉዳይ አይተው የሚወስኑት በሕግ መሠረት ነው። የግልግል ዳኞች የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች አይተው መወሰን ያለባቸው በሕግ መሠረት ከሆነ ደግሞ የግልግል ዳኞች የሠለጠኑ ይሁኑ ወይም በልምድ ብቻ የሚሠሩ ይሁኑ የሕግ ባለሙያዎች መሆን ያለባቸው ይመስላል።

በሌላም በኩል ከፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 15(2) በስተጀርባ ያለው ሀሳብ በነኚሁ በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር በተዘረዘሩት ጉዳዮች አካባቢ ያሉት ሕጎች አተረጓጎም አንድ ወጥ እንዲሆንና ወደፊትም በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የሚነሱት ክርክሮችም በምን አቅጣጫ እንደሚወሰኑ አስቀድሞ እንዲታወቅ

ለማድረግ ከሆነ ግን በቁ. 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚነሱ ክርክሮች በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ተፈልጎአል የሚለው አቋም ባጠቃላይ መልኩ ልክ ሊሆን ይችላል።[17] በሌላ መልኩም በኢትዮጵያ ውስጥ የግልግል ዳኞች ጉዳዮችን የሚዳኙት በሕጎች መርሆች እስከሆነ ድረስ[18] ከነኚህ በቁጥር 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚነሱት ክርክሮች በግልግል ዳኝነትም ቢታዩ ይህን ያህል የጎላ ልዩነት አያመጣም ማለትም ይቻላል። ይሁን እንጂ በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 317(2) ሥር በተጻፈው መሠረት ተከራካሪ ወገኖች ከተስማሙ የግልግል ዳኞች ከሕግ ጥብቅ መመሪያ ወጣ ባለ መመዘኛ ክርክራቸውን ሊዳኙ እንደሚችሉ መመልከቱን መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። የግልግል ዳኞች ከሕግ ጥብቅ መመሪያ ወጣ ባለ መመዘኛ እንዲዳኙ ከተከራካሪ ወገኖች የሚሰጣቸው ሥልጣን (ፈቃድ) ኤክስ ኤኮ ኤ ቦኖ አሚያብል ኮምፖዚሽን (በፍትሕና በርትዕ በሚዛናዊነት) ተብሎ ይጠራል። ከደረቅ የሕግ መመዘኛ ወጣ ባለ መመዘኛ እንዲዳኙ (እንዲዳኝ) ሥልጣን የሚሰጣቸው (የሚሰጠው) የግልግል ዳኞች (ዳኛ) በፍትሕና በርትዕ በሚዛናዊነት የሚዳኝ (አሚያብል ኮምፖዚተር) በመባል ይታወቃል።

ምናልባት ተከራካሪ ወገኖች በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ሥር ለከፍተኛው ፍ/ቤት ለብቻ የተሰጠውን የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን በስምምነት ሊያስወግዱት አይቻልም ብሎ የመከራከር ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል እንዲዳኙ ለሰየሚቸው ዳኞች ከደረቅ ሕግ መመዘኛ ወጣ ባለ መመዘኛ እንዲዳኙአቸው ሲስማሙ ይህ ራሱ የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 15(2) ተፈጻሚ እንዳይሆን እንደማድረግ ሊቆጠር ይችላል። የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) መኖር በዚሁ ሕግ በቁጥር 315(2) ሥር ከተደነገጉት ሁለት ነጥቦች "በግልግል እንዳይወሰን የተከለከለ" በሚለው ነጥብ ስሚት ተከራካሪ ወገኖች ከነዚህ በፍ.ብ.ሥነ ሥርዓት ሕጉ በቁጥር 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚነሳውን ማንኛውንም ክርክር ለግልግል እንዲያቀርቡ ተከልክሏል ካልተባለ በስተቀር በቁ. 15(2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ቢያንስ ከጥቂቶቹ የሚነሱትን አለመግባባቶች ተከራካሪ ወገኖች ለግልግል ዳኝነት የማያቀርቡበት አሳማኝ ምክንያት ያለ አይመስለኝም።

ለመነሻ ያህል ለምሳሌ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁ.15(2)(ሐ) ሥር በተጻፈው መሠረት ከመድን ውል ፖሊሲዎች የሚነሱት ክርክሮች ለግልግል ዳኝነት እንዳይቀርቡ ምን የሚያግዳቸው ነገር አለ? ከመድን ውሎች የሚነሱ ክርክሮች ለግልግል እንዳይቀርቡ የሚያግድ ፖሊሲ ይኖር ይሆን? ከመድን ውል ፖሊሲዎች የሚነሱ ክርክሮች በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ሥር መጠቀሱ መድን ነክ ጉዳዮች ለግልግል እንደማይቀርቡ ያመለክታል ከተባለ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሲጠቀምባቸው በቆየባቸውና አሁንም በሚጠቀምባቸው በርካታ የመድን ውል ፖሊሲዎች ውስጥ የተካተቱት የግልግል ስምምነቶች[19] የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁ. 15(2) ድንጋጌን የሚተላለፉ ስለሆነ ተፈጻሚ

---

[17] በኢትዮጵያ ውስጥ የበላይ ፍ/ቤቶች በሚሰጡት ውሳኔ የበታቾቹ የመገደብ ወይም የበላዮቹ የሰጡትን ውሳኔ የመከተል ግዴታ እንደሌለ መገንዘቡ ጥሩ ነው።

[18] የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 3325(1)።

[19] ለምሳሌ ያህል Condition No. 14 of the Workmen's Compensation Policy, Condition No. 11 of the Housebreaking Insurance Policy (Forcible and Violent Entry Cover), **Condition** No. 11 of all Risks Policy, Condition No. 8 of the Money Policy ወዘተ ይመልከቱ።

መሆን የለባቸውም ሊባል ነው። ተዋዋይ ወገኖች የግልግል ስምምነትን የሚያመለክቱ የውል ቃሎች ያስገቡባቸው የመድን ፖሊሲዎች ተዋዋዮቹ የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደረጉበት ሁኔታን ከማመልከቱም በላይ በዚህ ዓይነቱ ስምምነት ተዋዋዮቹ ጉዳያቸውን ከመጀመሪያው የብቻ የሥረ-ነገር ዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው ለከፍተኛው ፍ/ቤት የማቅረቡን መብታቸውን በገዛ ፈቃዳቸው እንደተውት ያስቆጥራል። በርግጥ ሕግ አውጭው የመድንን ጉዳዮች በቁ. 15(2) ሥር እንዲካተቱ ያደረገበት ምክንያት ከመድን ሰጭዎችና ከመድን አገልግሎት ሸማቾች እኩል ካለመሆን በመነሳት የመድን አገልግሎት ሸማቾች ከመጀመሪያው ደረጃ ዳኝነት ጀምሮ የከፍተኛውን ፍ/ቤት ድጋፍና እገዛ እንዲያገኙ አስቦም ሊሆን ይችላል።

በሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 15(2) ሀ ሥር የማሕበራትን መመሥረት ፥ መፍረስና ሂሳባቸው መጣራትን አስመልክተው የሚነሱ ክርክሮችም ቢሆኑ ለግልግል ዳኝነት እንዳይቀርቡ የሚከለክል የፖሊሲ ምክንያት ይኖር ይሆን ? የሚል የጥርጣሬ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው። ይህን ንዑስ-ንዑስ ቁጥር ከመቅረጽ አኳያ የሕግ አውጭው ፍራቻ በግለሰቦችና በግዙፍ የሞኖፖሊ ኩባንያዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በግልግል የሚታዩ ከሆነ የ3ኛ ወገኖች ፍትሕ ይጓደላል ከሚል ይሆን? ፍራቻው ይህ ከሆነ በግልግል ዳኝነት የሶስተኛ ወገኖች መብትና ፍላጎት አይጠበቅም ማለት ነው ወይንስ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውን ማሕበራትን/ድርጅቶችን የማቋቋሙ የማፍረሱና ንብረታቸውን የማጣራቱ ጉዳይ በውስጡ "መንግሥትን ፥ የመንግሥት ክፍላተ ሀገሮችን ፥ ሚኒስቴሮችንና የሕዝብ አስተዳደር ባለሥልጣናትን"[20] ያቀፈውንና "የአስተዳደር አካላት" በሚል አጠቃላይ መጠሪያ የሚታወቀውንም ስለሚጨምር ነው ? መንግሥትን ፥ የመንግሥትን ክፍላተ ሀገሮችን ሚኒስተሮችንና የሕዝብ አስተዳደር ባለሥልጣናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለምን ለግልግል እንደማይቀርቡ ግንዛቤ መውሰድ ቢቻልም ከግል ማሕበራት መቋቋም ፥ መፍረስ ወይም ንብረት ማጣራት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች ለምን ለግልግል እንደማይቀርቡ ግን አነጋጋሪ መሆኑ የማይቀር ነው።

ከዚህ በፊት[21] እንደተነሳው የፈረንሳይ ሕግ የግልግል ዳኝነትን ከሚከለክልባቸው የተለዩ ጉዳዮች ውስጥ "የሕዝብ የጋራ የሆኑና የሕዝብ ተቋሞችን" የሚመለከቱ ክርክሮች አንዱ ክፍል ናቸው። እነኚህ ከዚህ በላይ በተመለከተው ጎራ የሚመደቡና "የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች የተከለከሉባቸው ጉዳዮች መንግሥትና የመንግሥት አካላት ከተሳተፉባቸው ጉዳዮች የሚነሱትን ክርክሮች በግልግል እንዲታዩ ለማድረግ ችሎታ እንደሌላቸው ተደርጎ መተርጎሙ ሊሠመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው"[22] ይላሉ ሚስተር ካርቦኖ።

---

20 የፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 394 እስከ 397 ይመለከቷል።

21 በዚሁ ጽሁፍ ውስጥ በ 102 ኛው ገጽ ላይ የተባለውን ይመለከቷል።

22 Thomas Edgar Carbonneau, "The Elaboration of a French Court Doctrine on International Commercial Arbitration. A study in Liberal Civilian Judicial Creativity," 55 Tulane Law Review, 1980 ገጽ 9።

በብዙ አገሮች ከፓተንትና ከንግድ ምልክቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም በግልግል አይዳኙም[23] በንግድ ከመክሠር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም በበርካታ አገሮች በግልግል እንደሚታዩ ተደርገው አይወሰዱም።[24] በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 15(2)(ለ) እና (መ) ሥርም እነኚህ ጉዳዮች የተጠቀሱ ቢሆንም በዚህ ቁጥር ሥር መካተታቸው ግን በግልግል ዳኝነት እንዳይታዩ ለማገድ መሆን አለመሆኑ እንደሌሎቹ ጉዳዮች ሁሉ የሚያነጋግር ነጥብ ነው።

በባሕርላይ ከሚደረጉ ግንኙነቶች የሚነሱ አለመግባባቶች እንደዚሁም በሚተላለፉ ሰነዶች ላይ የሚነሱ ክሶች ለምን በግልግል ከመዳኘት ውጭ እንደሚሆኑ ለመገመት ያስቸግራል። የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 15(2) ባጠቃላይ በቁ.15(2)(ለ) ሥር የተጻፈው በተለይ በግልግል ያለመዳኘትን የሚያመለክት ከሆነ በባሕር ሕግ ቁጥር 209[25] ሥር የተጻፈው ምን ትርጉም ሊሰጠው እንደሆነ ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል። በእንግሊዝ አገር ባሕር ነክ የሆኑ ጉዳዮች ለዚሁ ተብሎ በተለይ ለተፈጠረው የግልግል ዳኝነት ሥርዓት የሚታዩ ሲሆን ባሕር ነክ ጉዳዮችን ብቻ የሚዳኝ በለንደን "ዘ ለንደን ማሪታይም አርቢትሬሽን አሶስዬሽን" (ኤል ኤም ኤኤ) የሚባል ተቋቁሞ ይሠራል።

ከሚተላለፉ ሠነዶች የሚነሱ ክርክሮች ወይም ከነርሱ ጋር የተሳሰሩ ጉዳዮች ሲታሰቡ ከእነኚህ ሰነዶች የሚነሱ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት የማይታዩበት ምክንያቱ ምን ይሆን የሚል ጥያቄ አብሮ መነሣቱ አይቀርም። እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በ1920 ከተፈረመው የጄኔቫ ፕሮቶኮል ጀምሮ (ቢያንስ ለዓለም አቀፍ ግልግል) በግልግል ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች "...ንግድ ነክ የሆኑ ወይም ሌሎች በግልግል ሊያልቁ የሚችሉ"[26] ተብለው ተገልጸዋል። መመዘኛው ይህ በ1923ቱ የጄኔቫ ፕሮቶኮል የተቀመጠው ከሆነ ከሚተላለፉ ሰነዶች የሚነሱ ጉዳዮች ለግልግል አይቀርቡም የሚያሰኝ ምክንያት ያለ አይመስልም። ለነገሩ የሚተላለፉ ሠነዶች ከራሱ ከተፈጥሯቸው ቢሆን ዋንኛ ንግድ ነክ ናቸው።[27] በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 715(2) መሠረት "የንግድ ወረቀቶች" ከሚባለው ክፍል ውስጥ የማይደመሩ "የግዴታ ምስክር ወረቀቶች" እና "የሸቀጥ ማረጋገጫ ሠነዶችስ" ቢሆኑ በክርክር ንግድ ነክ ሰነዶች አይደሉም ሊባሉ ነው ? እኔ በግሌ እጠራጠራለሁ። በርግጥ "የግዴታ ምክክር ወረቀቶች" እና "የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶች" የሚባሉት በኢትዮጵያ ሕግ የንግድ ወረቀቶች ዋና መለያ የሆነውን "ሐተታ የሌለበት የገንዘብ ክፈል ትዕዛዝ

23 Rene David, Arbitration in International Trade, Kluwer Deventher, Netherlands, 1985 ገጽ 188። በተጨማሪም Redfern and Hunter በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተውን ገጽ 106፣ እንዲሁም Craig Park and Paulson, International Chamber of Commerce Arbitration, Oceana Publication Inc., 1986, Vol. I part II Chapter 5, section 07 ይመልከቱ።

24 Craig Park and Paulson, International Chamber of Commerce Arbitration, Oceana Publication Inc., 1986, Vol. I part II, chapter 5, Se^tion 07.

25 በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የባሕር ሕግ ቁጥር 209 ይመለከቷል።

26 Redfern and Hunter በማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተው ፣ ገጽ 104።

27 በኢትዮጵያ በንግድ ሕግ ውስጥ መካተታቸው እንደዚሁም በUnited States of America "Commercial Papers" ተብለው መጠራታቸው ለዚሁ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይገመታል።

ወይም ሐተታ የሌለበት የገንዘብ እከፍላለሁ ትስፋ"[28] ይዘው የሚሄዱ ሰነዶች አይደሉም። የገዘብ ክፈል ትዕዛዝ ወይም እከፍላለሁ ተስፋ የመያዛቸው መመዘኛ ሲቀነስ የግዴታ ምስክር ወረቀቶች "ግዙፍነት የሌላቸው ከኩባንያ ወይም ከባለአደራ ወይም ከሌላ ንብረት ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ማረጋገጫ ወይም ከነኚሁ ከሚከፈል ክፍያ ለማግኘት የባለመብትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ናቸው። ቢሆንም በዘመናዊ የንግድ ግንኙነቶች ውስጥ እንደማንኛውም ግዙፍነትና ሀልዎት እንዳላቸው እቃዎች ወይም እንደተራ የንግድ ሸቀጦች ይሸጣሉ ፥ ይገዛሉ ፥ ይተላለፋሉ።"[29] በዕዳ ወይም በባለዕዳነት ወይም በንብረት ማረጋገጫ ሰነድነታቸው የሚተላለፉ የግዴታ ምስክር ወረቀቶች የሚባሉት እንደ ዕዳ ሠነዶች (ቦንድስ) የአክሲዮን ሰርተፊኬቶች እና የግዴታ ወረቀቶች (ዲበንቸርስ) እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።[30] የሚተላለፉ ሠነዶችን በሚመለከቱ ሌሎች ጽሁፎች "ከግዴታ የምስክር ወረቀቶች" (ሰኪዩሪቲስ) ጋር ብዙ ጊዜ "ኢንቨስትመንት" የሚል ቃል ከሰኪዩሪቲስ ቀድሞ ተጽፎ ይታያል። በመሆኑም በኛ የንግድ ሕግ ውስጥ "የሚተላለፉ የግዴታ ምስክር ወረቀቶች" የተባሉት በሌሎች ጽሁፎች "ኢንቨስትመንት ሰኪዩሪቲስ" (ኢንቨስትመንት ምስክር ወረቀቶች ?) ተብለው ተጽፈው ይነበባሉ።[31]

"የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶች" የሚባሉት ሌሎች ትርጓሜዎች ሊኖራቸው ቢችልም ከሕግ አንፃር ዕቃ የተላከለት ሰው ዕቃዎቹ ገና አጓጓዥ እጅ ወይም በጉዞ ላይ እያሉ በጀርባቸው ላይ በመፈረምና ለሚፈልገው ሰው በማቀበል ዕቃዎቹን ሊሸጣቸው የሚያስችሉ ለተላከለት ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ናቸው[32] ተብለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ። የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶች ዕቃዎች ተልከውልኛል ለሚለው ሰውም የዕቃዎቹ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

በዘመናዊ የንግድ ሥራ ውስጥ የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነድ የሚባለው ጅምላ አጠራር ዕቃዎቹ በባሕር፥ በአየር ፥ ወይም በባቡር መጓጓዛቸው ላይ ተመሥርቶ ቢል ኦፍ ሌዲንግ ፥ ኤር ዌይ ቢል እና ሬል ዌይ ቢልን ያጠቃልላል።

የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዕቃዎች ሽያጭ ግዥና መጓጓዝ ጋር የተቆራኙ እስከሆኑ ድረስ እነዚህንም ሰነዶች ከንግድ ግንኙነቶች ወይም እንቅስቃሴዎች ውጭ መመደብ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህም ከንግድ ወረቀቶች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ

---

28 በ1952 ዓ.ም የወጣውን የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 732(ሐ) ፥ 735(ለ) ፥ 823(ለ) እና 827(ሀ) ይመለከቷል።

29 79 Corpus Juris Secundum, Security, Securities, ገጽ 946።

30 ዝኒ ከማሁ ገጽ 945።

31 ለምሣሌ ያህል Uniform Commercial Code የተሰኘውን ሕግና በርሱ ላይ የተጻፈውን ይመልከቱ።

32 Clive M. Schmitthoff, The Export Trade The Law and Practice of International Trade, Stevens and Sons Ltd., London 6th ed., 1975 የተለያዩ ገጾችን ይመልከቱ።

በሚተላለፉ ሠነድነት ዕውቅና የተሰጣቸው የግዴታ ምስክር ወረቀቶችና የሸቀጥ ማረጋገጫ ሰነዶችም ቢሆኑ አገልግሎታቸው ከንግድ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ውጭ እስካልሆነ ድረስ ከሶስቱም የሚተላለፉ ሠነዶች ክፍሎች የሚነሳ ማንኛውም ክርክር በግልግል ዳኝነት የማይታይበት ምክንያት ያለ አይመስልም።

በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁ. 15(2)(ሠ) እና (ረ) ሥር የተመለከቱት ጉዳዮችስ እንዴት ነው የሚታዩት ? "ንብረትን አስለቅቆ ለሕዝብ ጥቅም ከማዋል" ጋር የተያያዙ አለመግባባቶችና ክርክሮች ሁሉ በኢትዮጵያ ውስጥ በግልገል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉ ነው መወሰድ የሚገባቸው ? ንብረትን ማስለቀቅ ችሎታ ያለው አንድ የመንግስት ባለሥልጣን የሚወስደው እርምጃ ውጤት እስከሆነ ድረስና "ባለሥልጣን"[33] ማለት ደግሞ እንደ "አስተዳደር አካል"[34] እስከተወሰደ ድረስ ምናልባት "ንብረትን ከማስለቀቅ" ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በግልግል ሊታዩ አይችሉም ብሎ መከራከር የሚቻል ሲሆን ባለሥልጣን ንብረት በማስለቀቁ ጥቅም ተነክቶብኛል የሚለው ግለሰብ ንብረት ማስለቀቁ ከተገቢው ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ውጭ ነው የተደረገው ወይም የሕግን ሥርዓት ባልተከተለ ሁኔታ ነው የተከናወነው በማለት አቤቱታውን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል ተብሎ ሲገመት ከዚህ ውጭ ሥልጣን ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን ባግባቡ በወሰደው የንብረት ማስለቀቅ እርምጃን ወይም ውሳኔን የተወሰደው ንብረት ባለቤት ባለመቀበሉ ምክንያት የሚፈጠረው አለመግባባት "መንግስት በግልግል አይዳኝም።"[35] (ሶቭሬን ኢምዩኒቲ) በሚባለው መርሕ መሠረት ከግልግል ውጭ ይሆናል ለማለት ይቻላል። ሆኖም ንብረትን ከማስለቀቅ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በግልግል አይታዩም ቢባልም እንዲለቀቅ ለተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት በሚከፈለው የካሣ መጠንና አከፋፈልን እንደዚሁም ሶስተኛ ወገኖች በአስለቃቂው መ/ቤት ላይ የሚያነሷቸው የመብት ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ክርክሮች ወይም አለመግባባቶች ግን በግልግል ዳኝነት ሊታዩ እንደሚችሉ መገንዘብ መልካም ነው።[36]

ሥልጣን ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን ያስለቀቀውን ንብረት ወይም ሌላም ንብረት ቢሆን "ለሕዝብ የጋራ አገልግሎትና ጥቅም ከማዋል" ጋር ተያይዘው የሚነሱ ክርክሮችስ ? ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች በግልግል ከመታየት ውጭ የሚያደርግ የፖሊሲ ምክንያት ይኖር ይሆን ? ጉዳዩ የሚያገባቸው ወገኖች ሁሉ ወደው ከተስማሙበት ንብረትን በጋራ ከመጠቀም የሚነሱ ክርክሮች ለምንድነው በግልግል ዳኝነት የማይታዩት ? ንብረትን በጋራ ከመጠቀም የሚነሱ ክርክሮች በግልግል እንዳይታዩ የሚደረግበት አንዱ ምክንያት ጉዳዩ ከሚያገባቸው ሰዎች ብዛት የተነሣና ምናልባትም ንብረቱ ባጠቃላይ ለሕዝብ የጋራ አገልግሎት ከዋለ በግልግል የሁሉንም ያገባኛል ባይ ጥቅምና ፍላጎት በፍትሐዊነት ማስከበር ስለሚያስቸግር

33 የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 1460 ይመለከቷል።

34 ዝኒ ከማሁ ከቁጥር 394 እስከ 397 ያሉትን ይለመከቷል።

35 Rene David, ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 23 የተመለከተው ከገጽ 175-180 እንዲሁም Redfern and Hunter ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተው ከገጽ 110-111፣ Craig Park and Paulson ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተመለከተውን Vol.I. Part VI chapter 36 section 03 ይመልከቱ።

36 የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1467(3) ከቁጥር 1472 እና ተከታታዮቹ ተጣምሮ።

ነው ለማለት ይቻላል። በመሆኑም የያገባናል ወገኖች መብዛትና የእያንዳንዱን ያገባኛል ባይ ወገን ፍላጎትና ጥቅም ለማስጠበቅ በሚደረገው ጥረት የሚፈጠረው ውስብስብ ሁኔታ ራሱ ከዚህ ሁኔታ የሚነሱ ነገሮች ለግልግል እንዳይቀርቡ ለማድረግ በቂ የፓሊሲ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ከዚህም በላይ ለፍትሕ ሲባል ክርክሮችን ማጣመር ተፈላጊ ቢሆንም እንኳን ባንድ ጉዳይ ያገባናል የሚሉትን ወገኖች ክርክር ሁሉ ለማጣመር ወይም ለማዋሀድ አንድ የግልግል ዳኝነት መድረክ ሥልጣን የለውም[37] ይባላል። አንድ ችሎታ ያለው የመንግሥት ባለሥልጣን ያስለቀቀው ንብረት ለሕዝብ የጋራ ጥቅም ወይም አገልግሎት ከዋለ ደግሞ ከእንዲህ ዓይነት ንብረት ተጠቃሚዎች ወይም ተገልጋዮች የሚነሳው ክርክር ለግልግል አይቀርብም የሚያሰኝ ጠንካራ የፖሊሲ ምክንያት አለ ለማለት ይቻላል።

በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.15(2)(ረ) ሥር የተጻፈውና "የመንግሥት ሠራተኞች በሥራቸው ምክንያት የተሰጣቸውን አላፊነት በማጓደል' ላይ ተመሥርተው የሚነሱ ክርክሮች ለግልግል ዳኝነት እንዲቀርቡ አለመፈለጉ "መንግሥት አይከሰስም" በሚለው መርሕ የተሸፈነ ነው ለማለት ይቻላል። ርዕሱ "ስለመንግሥት አላፊነት" በሚለው በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2126[38] ውስጥ በተለይም በንዑስ ቁጥር(2) ሥር የሚከተለው ተደንግጎአል።

> የተደረገው ጥፋት የመንግሥቱን ሥራ ሲሠራ የደረሰ የሥራ ጥፋት የሆነ እንደሆነ የተጎዳው ሰው ኪሣራ ከመንግሥት ላይ ለመጠየቅ ይችላል። ሆኖም ስለከፈለው ገንዘብ መንግሥት የተባለውን ሠራተኛ ወይም ሹም መልሶ እንዲከፍለው ለመጠየቅ መብት አለው።[39]

በዚህ ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ መሠረት በዚህ የሕግ ቁጥር ሥር ለሚነሱ (ሁሉም ማለት ይቻላል) ክሶች መንግሥት ተከሣሽ እንደሚሆን ግልጽ ነው።[40] እንደዚሁም በፍ.ብ.ሕ.ቁ.2128 ሥር የቀደሙት ሁለት ቁጥሮች ድንጋጌዎች በክፍላተ ሀገራት በሚሠሩ የመንግሥት ሠራተኞችና ፥ በሕግ የሰውነት መብት

---

37 Redfern and Hunter ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተው ገጽ 19 ይመልከቱ።

38 ሕግ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ከሚያስገድዳቸው ሁኔታዎች ውጭ ግልግል የሚነሣው ከውል እንደመሆኑ መጠን ከውል ውጭ ግዴታዎች የሚነሱ ክርክሮች በግልግል ሊታዩ ስለመቻላቸው አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። በሌላም በኩል መንግሥት ወይም የክፍላተ ሀገራት የመንግሥት አስተዳደር ክፍሎች የተሳተፉበት ጉዳይ ምናልባትም የመንግሥትን ውሎች የሚዋዋሉ ባለሥልጣናትን አላፊነት በሚመለከት በፍ.ብ.ሥ.ሥ ሕገ ቁጥር 315(2) ሥር ከተጻፈው ሌላ የሚመራን ድንጋጌ የለም።

39 George Krzeczunowicz, <u>The Ethiopian Law of Extra Contractual Liability</u>, Addis Ababa, Faculty of Law 1970, ገጽ 174 175 ይመልከቱ (ፕሮፌሰሩ ከውል ውጭ አላፊነትን የሚመለከቱ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥሮችን አሻሽለው ተርጉመው ለዚህ መጽሐፍ ቅጥያ ካደረጉት የተወሰደ።

40 በጥፋቱ በሌሎች ላይ ጉዳት ከሚያደርስ ባለሥልጣን ፥ ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም የሕዝብ አገልጋይ መንግሥት በገንዘብ አቋሙ በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛል ተብሎ ይገመታል።

በተሰጣቸው ያስተዳደር ክፍሎችና መ/ቤቶች በሚሠሩ ሠራተኞችም ላይ ተፈጻሚ መሆናቸውን ይደነግጋል።[41]

በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.15(2)(ሰ) ዜግነትን ፥ (ሸ) መወለድንና (ቀ) አካልን ነፃ ማውጣትን አስመልክተው የሚነሱ ክርክሮች ምናልባት በግልግል ከመዳኘት ውጭ በሚደረጉ ጉዳዮች ጎራ ውስጥ ይወድቃሉ ማለት ይቻላል። በነኚህ ሶስት ጉዳዮች ላይ የሚመሠረቱት ክሶች ጉዳዩን ከሚመለከቱ ሕጎች የሚነሱና አቤቱታ አቅራቢው የራሱን ጥቅም ለማስከበር የሚያቀርባቸው ናቸው።[42] ቢሆንም በነዚህ ጉዳዮች ላይ በሚቀርቡት ክሶች የሚሰጡት የመጨረሻ ውሳኔዎች መንግሥትንም ሆነ ሕዝብን የሚነኩ ስለሆነ ሁለቱም በነዚህ ጉዳዮች ላይ ጥቅም አላቸው ለማለት ይቻላል። ዜግነት "አንድ ሰው ላንድ ለተለየ አገር ታማኝነቱን የሚገልጽበት የፖለቲካ አቋም"[43] እንደመሆኑ መጠን ይህ ብቻውን ዜግነትን የሚመለከቱ ክሶች በተከራካሪ ወገኖች የግል ዳኞች እንዳይታይ ለመከልከል በቂ የፖሊሲ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በመሠረቱ "የወላጅና የልጅ ዝምድና"[44] ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለውን መወለድንም የሚመለከቱ ክሶች ወይም ክርክሮች በግልግል የሚታዩ አይደሉም ብሎ መከራከር የሚቻል ይመስለኛል። በመወለድ ክሶች የመጨረሻ ውጤት ላይ ሕብረተሰቡም ጥቅም ያለው ነው ለማለትም ቢቻል ሕጉም ቢሆን በተቻለ መጠን ልጆች ያለአባት ወይም እናት እንዳይቀሩ እንዲደረግ ከመፈለጉ[45] አኳያም ሲታይ የመወለድ ክሶች በፍ/ቤቶች እንጂ በግልግል እንዳይታዩ መፈለግን ያንፀባርቃል ለማለት ይቻላል። በነገራችን ላይ ቤተሰብ ነክ ከሆኑ ጉዳዮች መወለድን የሚመለከቱ ብቻ ይመስላሉ በግልግል ዳኝነት ከመታየት ውጭ የተደረጉት። ሌሎቹ ቤተሰብ ነክ ጉዳዮች በተለይም ፍቺና ከፍቺ ጋር የተያያዙት በግልግል ዳኝነት መታየታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የግድ[46] እንጂ በተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት ወይም ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ አይደሉም።

---

41 የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 394 እና ተከታታዮቹን ይመልከቱ።

42 በርግጥ አንዳንድ ጊዜ እነኚህን ጉዳዮች የሚመለከቱ አቤቱታዎች በሌሎች አማካኝነትም ሊቀርቡ ይችላሉ። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የአቤቱታ ማመልከቻ የሚያቀርቡ ሰዎች ግን ባብዛኛው በባለጉዳዩ ስምና ምትክ ሆነው የሚያቀርቡ ይሆናሉ።

43 Cheshire and North, Private International Law 11th ed., Butterworths, London, 1987 ገጽ 168።

44 36 Corpus Juris Secundum ገጽ 404።

45 የጎሊና ግምት የሚጥሉትን ከ741 እስከ 745 ያሉትን የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥሮች ይመልከቱ።

46 በተጨማሪም ከ725 እስከ 737 ያሉትን የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥሮች ይመልከቱ። ነገር ግን በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 730 መሠረት ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮች በግልግል እንደማይታዩ ልብ ማለት ይገባል።

አንድ ሰው ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ያለውን አቋም የሚያመለክቱ እንደ መወለድ ዜግነት ወዘተ ያሉት ጉዳዮች ባጠቃላይ በግልግል ዳኝነት እንደማይታዩ ጉዳዮች ይቆጠራሉ።[47] ቤተሰብ ነክ ጉዳዮች በበርካታ ሀገሮች ሕጎች በግልግል ዳኝነት እንደማይታይ ጉዳዮች ሲቆጠሩ[48] በዚህ ረገድ የኛ ሕግ ለየት ያለና ልዩነቱም በግምት ወግና ባሕልን የተመረከዘ ነው ለማለት የሚቻል ይመስለኛል።

አካልን ነፃ ለማውጣት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ አይችሉም ብሎ በርግጠኛነት መናገር ይቻላል። ሮበርት አለን ሴድለር በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 177 ላይ ተመሥርተው ሲጽፉ አካልን ነፃ የማውጣት ክሶች ባብዛኛው የሚቀርቡት "ወንጀል ሠርተሀል በመባል በቁጥጥር ሥር ባለ ሰው ሆኖ ክሶቹም የሚመሠረቱት ትዕዛዝ ለማሰጠት ሲሆን የሚታዩትም እንደ ፍትሐብሄር ክስ ነው"[49] ይላሉ። ብዙ ጊዜ ያሠረውን ሰው ይዞ ፍ/ቤት እንዲቀርብ የሚታዘዘው ባለሥልጣን ትዕዛዙን ላያከብር ይችላል የሚል ስጋት ከበስተጀርባ ስለሚኖር አስገዳጅ የመንግሥትን ከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን የሚያስፈልገውም ከዚህ ሁኔታ አንፃር ነው።በመሆኑም አካልን ነፃ የማውጣት ክሶች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ ከሚችሉት ጉዳዮች ውጭ ቢደረጉም ምክንያቱን ማወቁ አስቸጋሪ አይሆንም።

6

## በግልግል ዳኝነት ይታያል አይታይም ተያቄና በሕግ ፊት የሚፀና ውል ጉዳይ።

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ውስጥ በግልግል ዳኝነት ስለሚታዩና ስለማይታዩ ጉዳዮች በቂ መርሆች እስከሌሉ ድረስ ተጨማሪ የአተረጓጎም ጥረቶችን ማድረግ አስፈላጊ ነው እላለሁ። በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.315(2) ከተጻፈውና ሕግ የግልግል ዳኝነቱን የግዳጅ ከሚያደርግባቸው ሁኔታዎች ውጭ የተፈጠረውን አለመግባባት ይሁን ወደፊት የሚፈጠረውን በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ ማድረጉ የሚነሳው ከውል ነው። ግልግል ከውል የሚመነጭ ከሆነ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1676 መሠረት ልዩ የሆኑት ከቁጥር 3325 እስከ 3346 ያሉት የዚሁ ሕግ ቁጥሮችና ምናልባትም የፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.

---

47 Carbonneau ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 22 የተመለከተው ገጽ 9 ፤ እንደዚሁም Redfern and Hunter በማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተውን ገጽ 105 ፤ Rene David ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 23 የተመለከተውን ገጽ 187 ይመልከቱ።

48 Redfern and Hunter በማስታወሻ ቁጥር 1 የተመለከተው ገጽ 105 106 Rene David ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 23 የተመለከተው ገጽ 187

49 Robert Allen Sedler, Ethiopian Civil Procedure, Faculty of Law, Haile Sellasie I University, 1968 ገጽ 28 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 36 ይመልከቱ።

ከቁጥር 315 እስከ 319 ያሉት አልፎም የዚሁ ሕግ ቁጥር 461 በልዩነታችሁ ተፈጻሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሎችን በጠቅላላ የሚመለከት ከቁጥር 1675 እስከ 2026 ያሉት የፍ.ብ.ሕ. ድንጋጌዎች በግልግል ውሎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ግልግልን የሚመለከቱ ስምምነቶች በጠቅላላ የውል ድንጋጌዎች የሚመሩ ከሆነ ለሚፀና ውል አስፈላጊ ናቸው ተብለው በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1678 ሥር የተመለከቱት:-

- ሀ) ውል መዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፤
- ለ) በቂ የሆነ እርግጠኝነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ፤
- ሐ) የዉሉ አጻጻፍ ፎርም ዓይነት በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈፀም ፈራሽነትን የሚያስከትል ሲሆን አንድ ልዩ ፎርም

የተሰኙት በግልግል ስምምነትም ላይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ።

በቁ. 1678 ሥር ከተመለከቱት ነጥቦች በንዑስ ቁጥር (ለ) ሥር የተካተተውና የአንድ ውል ጉዳይ በቂ የሆነ እርግጠኝነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ መሆኑን የሚደነግገው በግልግል ሊታዩ ከሚችሉና ከማይችሉ ጉዳዮች (አርቢትረቢሊቲ) ጥያቄን የሚመለከት አግባብነት ያለው ሁኔታ ነው። በቁ. 1678(ለ) ሥር የተጻፉት ሶስቱም ሁኔታዎች በግልግል ለመጨረስ በሚደረጉ ስምምነቶች ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው አጠራጣሪ ሲሆን ቢችልም በስምምነት ለመጨረሱ ስምምነት መሠረት የሆነውን ስምምነትን (ውልን) ለማስፈፀም ይ፣ ለመለወጥና ለመተርጎም ግን ሶስቱም ሁኔታዎች ተፈጻሚዎች መሆናቸው አከራካሪ "አይሆንም። በመሆኑም ከአመሠራረቱ ሕገ ወጥ ወይም የሕብረተሰቡን የሞራል ደንብ የሚቃረን ጉዳይ ያለበት ውል በግልግል ዳኝነት መታየት አይችልም ብሎ መከራከር ይቻላል። በሕግ ፊት የማይፀና እንደ ሕገ ወጥና የሞራልን ደንብ የሚያጎድፍ ጉዳይ ያላቸው ውሎች በግልግል ዳኝነት የሚታዩ ከሆነ ችግር የሚፈጠረው የግልግል ዳኝነቱ መድረክ በሚያስችልበት አካባቢ የፍ/ቤቶችን እገዛ ሲጠይቅ ነው። በሌላም በኩል ሕገ-ወጥ የሆነ ጉዳይ ካለው ውል በተነሣ ክርክር ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ለግልግል ዳኝነት አቅርበው ውሳኔ ቢያሰጡም የተረታው ወገን ውሳኔውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ ረቺው ወገን ለውሳኔው አፈጻፀም ለፍ/ቤት ቢያመለከት ማመልከቻው የቀረበለት ፍ/ቤት ሕገ-ወጥ ወይም የሞራልን ደንብና ወግ ከሚጥስ ስምምነት የተገኘውን ውሳኔ ለማስፈፀም እምቢ ሊል ይችላል፤ ሊልም ይገባል።

## 7 መደምደሚያ

በጥያቄ ልደምድም። በኢትዮጵያ ውስጥ በፍ.ብ.ሕ. ከቁጥር 3325 እስከ 3346 የተጻፉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሕግ በተለይ ያልከለከለው ማንኛውም ክርክር በሕግ ፊት ከሚፀና ውል ወይም ከሌላ ሕጋዊ ግንኙነት[50] እስከመነጨ ድረስ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚችል ይመስላል?

50 በፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 3328(3) ሥር የተመለከተው አገላለጽ "... በተለየ የመብት ግዥነቱ ..." ቢሆንም ከተጻፈው ይልቅ የሕግ አውጭው ሐሳብ በተሻለ የሚያንጸባርቀው "ከአንድ ከተለየ ሕጋዊ ግንኙነት" ቢባል ነው ብዬ አስባለሁ።